***በሚኔሶታ በሊቢያ፣ በደቡብ አፍሪካና በየመን የተገደሉ ዜጎቻችንን በሚመለከት የጸሎትና የሻማ ማብራት ስነሥርዓት ተደረገ።***

*ዛሬ ሚያዝያ 15 ቀን 2007 ዓ.ም ከቀኑ 5፡00 – 8፡20 ፐም ባለው ጊዜ በሚኔሶታ የሚገኘው ኢትዮጵያውያን በሴንትፓውል ከተማ በሚገኘው እስቴት ካፐቶል( ቤተመንግስት) ፊት ለፊት ሴቶች በሙሉ የሐዘን ልብስ ጥቁር ልብስ በመልበስና እያለቀሱ ፤አንዳንድ ወንዶችም ጥቁር ልብስ በመልበስ በሚኔሶታ ታሪክ ለመጀመሪያ ጊዜ ወደ ሺ የሚገመት ሕዝብ በመሰብሰብ ዜጎቻችን በሊቢያ በተለያዩ ሁለት ቦታዎች የአይ ኤስ አይ ኤስ( ISIS) አንዱ ክንፍ በሆነው ደዬስ በተባለው አሸባሪ ቡድን አንገታቸው እየተቀላ እንዲሁም በኋላ በኩል በእሩምታ ተኩስ እንዲገደሉ መደረጋቸውን በመቃወም፣ በደቡብ አፍሪካ ደግሞ ኢትዮጵያና የኢትዮጵያ ህዝብ ያደረገውን ውለታ የራሱ ግለሰቦች በአገሪቱ በሚገኙ ስደተኛ ኢትዮጵያውያን ላይ በአንገታቸው ጎማ ተጠልቆ በጎማው ላይ ቤንዚን ተርከፍክፎ እንዲቀጠሉና እንዲሞቱ መደረጋቸውን በመቃወም እንዲሁም በየመን በዜጎቻችን ላይ የተፈጸመውንና እየተፈጸመ ያለውን ዘርፈ ብዙ በደል በመቃወም የተሰማቸውን ትልቅ ሀዘን የጸሎትና የሻማ ማብራት ሥነሥርዓት በማካሄድ ገልጸዋል። በሁሉም ኢትዮጵያዊ ፊት ይታይ የነበረው ንዴት ልዩ ነበር። በወገኖቻችን ላይ የሚደረሰው ጥቃትስ መቼ ነው የሚቆመው በማለት በመንግሥት ስም በተቀመጠው የወያኔ ስርዓት ላይ በመተባበር ትግል ማካሄድ እንደሚያስፈልግ ይነጋገሩ ነበር።*

*በዚህ ሥነሥርዓት ላይ በከተማው ውስጥ የሚገኙ የክርስቲናና የሙስሊም እምነት አባቶች ተገኝተው በወገኖቻችን ላይ የተፈጸመውን ግድያ ከመቃወማቸውም በላይ ለሞች ቤተሰቦች እ/ር ወይም አላሕ መጽናናትን እንዲሰጣቸው ጠይቀዋል። ጸሎትም አድርገዋል። የቅዱስ ራጉኤል ቤተክርሲያን አባት ስለችግሩ ማውራት እናብቃ በማለት “አበካችሁን ኢትዮጵያን እናስቀድም” ብለው ከተነገሩ በኋላ በሀዘኑ ቦታ ላይ የነበሩት አብረው እንዲሉ በማሳሳብ ሕዝቡም በመተባበር ያሉትን አሳምፏል።ቀጥለውም ኢትዮጵያ አገራችን ለአለበት ችግሮች መፍትሄዎቹ 1. ኢትዮጵያና ኢትዮጵያዊነት ማስቀደም፣ 2. ዘረኝነትን ማቆም 3. በአምላካችን ፊት ሁልጊዜ ስለ አገራችን መጸለይ ብለዋል። የለበሰነው ጥቁር ጨርቅ ሳይሆን ውርደት ነው። ይህን የውርደት ሁኔታ ለማስወገድ ቤተክርስቲያን ፣ በመስግዶችና በሌሎች ቦታዎች የሚደረገው ክፍፍል መቆም እንዳለበት አሳስበዋል። በአንድነት ቁሙ ብለዋል። እንዲሁም የቅዱስ ደብረ ሰላም መድኃኔዓለም ቤተክርስቲያን ሊቀመንበር የወያኔ መንግስት በሊቢያ የተቀሉ ዜጎቻችንን በሚመለከት ኢትዮጵያዊ መሆናቸውን እያጣራን ነው ብሎ የተነገረውን በጽኑ ተቃውማዋል። እንዲህ በማለት “ነብር ዥንጉርጉርነቱን ኢትዮጵያዊ መልኩን አይቀርም“ የተባለውን ብእል አንስተው የተቀሉትን ወገኖች መልካቸውን አይቶ የዜግነት ግዴታውን ያልተወጣው የወያኔ መንግስት እኛን ላይወክልም ቆርጠን በመተባበር በትግል ይህን ዘረኛ ሥርዓት ማስወገድ ያስፈልጋል በማለት አሳስበዋል። በቦታው የነበረውም ሕዝብ ለሁለቱም ተነጋሪዎች ድጋፉን በጭብጨባ ገልጿል። የሞቱ ዜጎቻንን በሚመለከት በቅዱስ ደብረሰላም መድሃኔዓለም ቤተክርርስቲያን ከሚያዝያ 16 ቀን ጀምሮ ለሰባት ቀናት የጾምና የጸሎት ጊዜ መወሰኑንም አሳውቀዋል።*

*ከሁለት የእስልምና እምነት ተቋማት የመጡ ሁለት መሪዎች እኛ ኢትዮጵያውያን በእምነት ብንለይም አንድ አገር ያለን፣ እርስ በርሳችን የምንከባበር፣የምንዋዳድ፣ በዓሎቻችንን ለእምነቶቻችን ክብር በመስጠት የምናከብር፣ የአገራችንን ጠላት በጋራ የተዋጋን ወደፊትም የምንዋጋ ህዝብ ነን። ምንም ጊዜም የማንከፋፈል ነን። ዜጎቻችንን የገደሉ አሸባሪዎች እስላሞችን የማወክሉ ናቸው። በጋራ እንዋጋቸዋለን። በሊቢያ ውስጥ በዜጎቻችን ላይ የሞት አደጋ ያደረሱትን አሻባሪዎችን ለመቃወምና ለማውገዝ ነገ ሚያዝያ 16 ቀን 2007 ዓ,ም ከጧቱ 10፡00ሌም- 5፡00 ፐም የተቃውሞ ሰልፍ ስለተዘጋጀ መጥታችሁ ሰልፉን ተቀላቀሉ በማለት ጥሪ ሲያቀርቡ በቦታው የነበረው ኢትዮጵያዊ ድጋፉን በጭብጨባ ገልጿል።*

*ከዚያም የተለያዩ አገራዊ ስሜትን የሚገልጹ ቀስቀሽ የሆኑ ግጥሞች፤ መዝሙሮችና ጽሑፎች ቀርበዋል። ከቀረቡት ግጥሞች አንዱ በሕዝብ ጥያቄ ሁለት ጊዜ የቀረበው “የሰማዕቱ የመጨረሻ ሰዓት” በሚል ርዕስ በአንድ ክርሲቲያን ወጣት በሊቢያ አገር ከክርስቲያን መንድሞቹ ጋር አብሮ በአሻባሪዎቹ ለተገደለው ለጀማል ራሕማቶ ማስታወሻ ቀርቦ የነበረው ነው። ሌላው ከሚኔሶታ ከኢትዮጵያ ተማሪዎች ማህበር ተወካይ ተማሪ “ አገር ማለት” በሚል ርዕስ የቀረበው ነው።*

*ከደብረ ሰላም መድሃኔዓለም ቤተክርስቲያን በመጡ አባት ጸሎት በኋላ የሻማው ማብራት ሥነሥርዓቱ 8፡20ፐም ላይ ተካናውኗል።*

*ኢትዮጵያ ለዘለዓለም ትኑር*

*ሪፖርት አቅራቢ፡ ዳዊት ከሚኔሶታ*